# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 320 ሰኔ 20 2006 ገጽ 1


**ህወሃት መቃብር አፋፍ ላይ ሆኖ የሚደግስልንን የጥፋት ድግስ ለማምከን የየብሄረሰቡ ልሂቃን ሁሉ አንድ ላይ ሆነን ህዝባችንን እንድንታደግ ግንቦት 7 ለሁሉም የነጻነት ሃይሎች ጥሪውን ያቀርባል።**

**ግንቦት 7 በዚህ የህወሃት የጨለማ መንገድ ላይ የሚያበራውን የብርሃን ችቦ ይበልጥ በማብራት ላይ ይገኛል። ሁላችንም በምናገኘው የብርሃን ሃይል ጨለማው ላይ እያበራን ከማሳየት አልፈን ወደ መቃብሩ ልንገፋው ይገባል።**

**ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)**

## የተለያዩ አለማቀፍ ተቋማት ኢትዮጵያ ውስጥ አፈና ለመኖሩ ምስክርነታቸውን ሰጡ

የተለያዩ አለማቀፍ ተቋማት የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ እያደረሰ ባለው አፈና፣ ግድያና ማፈናቀል ላይ ያላቸውን ወቀሳ በመሰንዘር ላይ መሆናቸውን ዘጋቢያችን ከላከልን መረጃ ለማወቅ ተችሏል። አለማቀፍ ተቋማቱ አገዛዙ ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ማፈኑን፣ የነጻውን ሚዲያ ፣ የፖለቲካ ድርጅቶችንና የሲቪክ ማህበራት እንቅስቃሴዎችን መግታቱን በማመልከት አለማቀፍ መንግስታት ጉዳዩን በአንክሮ ይመለከቱት ዘንድ አሳስበዋል። በአገሪቱ ሰላማዊ ተቃውሞ ማድረግ በፍጹም አልተቻለም፣ ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ ሰዎችን ማሰር ፣ ማሰቃየት እና በእስር ቤቶች ውስጥ ሰቆቃዎችን መፈጸምም ተጠናክሮ ቀጥሏል በማለት የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ ዜጎችን በሀይል ከመኖሪያ ቀያቸው የማፈናቀሉን ተግባርም በተጠናከረ ሁኔታ ማስቀጠሉን አመልክተዋል።

በርካታ ጋዜጠኞች አገዛዙን በመተቸታቸው፣ የፖሊሲ ማሻሻል እና ለውጥ እንዲደረግ በመጠየቃቸው ገሚሶቹ ለስደት የተቀሩት ደግሞ በሽብርተኝነት ተከሰው የብዙ አመታት እስር ተፈርዶባቸዋል በእስር ቤት እየማቀቁ እንደሚገኙም ተገልጿል።

በመላ አገሪቱ የሚገኙ ንጹሃን ዜጎች የጉጅሌው ወያኔን አገዛዝ በመቃወማቸው ብቻ በቁጥጥር ስር እየዋሉ በአገዛዙ ቀጥረኛ የፌደራል ፖሊሶች በዱላ፣ በቦክስ፣ በጥፊ እንደሚመቱ፣ እጃቸው ከግድግዳ ጋር ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## ተመድ የወያኔን የሰብዓዊ መብት ጥሰት የሚያጣራ ቡድን እንዲልክ ተጠየቀ

የተባበሩት መንግስታት ልዩ አጥኚ ቡድን ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባና የጉጅሌው ወያኔ በአገሪቱ ውስጥ እያደረሰ ያለውን የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን እንዲመረምር መጠየቁ ታውቋል። በቅርቡ ከአዲስ አበባ ከተማ አዲስ ማስተር ፕላን ጋር በተያያዘ የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ በደረሰበት ተቃውሞ በተለያዩ የኦሮሚያ ግዛቶች በሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ላይ የወሰደው የሰብአዊ መብት ጥሰትን በተመለከተ የመንግስታቱ ልዮ አጥኚ ቡድን ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ሁኔታውን እንዲመረምር የተለያዩ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችና ከሁኔታው ጋር ግንኙነት ያላቸው ወገኖች በሳምንቱ መጨረሻ ላይ በፃፉት ደብዳቤ ጠይቀዋል። በኢትዮጵያ ውስጥ ገለልተኛ አጣሪ ቡድን የለም! የሚሉት እነዚህ ወገኖች ባለፈው ግንቦት 25 2006 ዓ/ም ከ 6 አመት የእስር ቆይታ በኋላ ህይወቱ ያለፈውን ወጣት ኢትዮጵያዊ አሚሚት፤ በእስር ቤት ውስጥ ያለውን የቶርቸርና ሰቆቃ ሁኔታን ያመላክታል ሲሉ እምነታቸውን ገልጸዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ በአሜሪካ የዋሽንግተን ግዛት የህዝብ ተወካዮች የሆኑት ሴናተር *ማርያ ኮንቶዌልና ሴናተር ፔቲ ማሪ* የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ውስጥ እያካሄደ ያለውን የሰብአዊ መብት ጥሰቶችና ረገጣወች እንዳሳሰቧቸው ሰኔ 12 2006 ዓ/ም ለውጭ ጉዳይ ሚኒስተር ጆን ኬሪ በላኩት ደብዳቤ ገልፀዋል። ሁለቱ ባለስልጣናት የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ለህግ የበላይነት እንዲገዛና የዋሽንግተን መንግስትም ግፊትና ጫና እንዲያደርግ አበርክረው መጠየቃቸው ታውቋል።

በቅርቡም የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ በንጹሃን ዜጐች ላይ እየፈፀመ ያለው የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንዳሳሰበው የሰብዓዊ መብት ተቆርቋሪ ተቋሙ አምኒስቲ ኢንተርናሽናል መጠየቁንም መዘገባችን ይታወሳል። ተቋሙ ባወጣው ዓመታዊ የሰብዓዊ መብት አጠባበቅ ሪፖርት በአፋኝ ህግጋቶች የተነሳ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች መንቀሳቀስ አለመቻላቸውን እና በመሬት ወረራው ምክንያት ብዙ ዜጐች ከመኖሪያቸው መፈናቀላቸውን በማንሳት በፋሽስቱ የወያኔ አገዛዝ ላይ ከፍተኛ ትችት ማቅረቡ ይታወሳል።

## ፋሽስቱ ወያኔ የመኢአድ አባላትን እስርና ግድያና እንደቀጠለበት ነዉ

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) በየቦታው በአባላቶቹ ላይ በጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ታጣቂዎች የሚፈጸመው ግድያና እስራት ተጠናክሮ መቀጠሉን በመግለጽ ድርጊቱንም በጽኑ እንደሚያወግዝ አስታውቋል። ባለፈው ሳምንት በምስራቅ ጎጃም ዞን ደንጎሊማ ቀበሌ የፓርቲው የቀበሌ ተጠሪ የነበሩት አርሶ አደር ሞላ አዳነ በአገዛዙ ታጣቂ ካድሬዎች ተደብድበው ህይወታቸው ማለፉን መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን የፓርቲው የወረዳው ምክትል ሰብሳቢ መቶ አለቃ ደመላሽ ጌትነት ትላንት ታትሞ ለወጣው አዲስ አድማስ ጋዜጣ እንደገለጹት፤ በታጣቂ ካድሬዎች የተገደሉት አርሶ አደር ሞላ አዳነ ቀድም ሲልም የተቃዋሚው መኢአድ አባል በመሆናቸው ብቻ በጉጅሌው ወያኔ ቅጥረኞች ሴራ ከእድርና ከቤተ ክርስቲያን ከመገለል አንስቶ በርካታ በደሎች ይፈጸሙባቸው እንደነበር ገልጸዋል። በመኢአድ አባላት ላይ እየተወሰደ ያለው ጥቃት በዚህ ያላበቃ መሆኑን የዘረዘሩት የወረዳው ምክትል ሰብሳቢ አያይዘውም በዚያው በነማይ ወረዳ ነዋሪ የሆኑ የመኢአድ አባል የሆኑት አቶ ይበልጣል ወንድሜነህ ቤትህ ውስጥ መሳሪያ ደብቀሃል በሚል በታጣቂዎች ታፍነው ከተወሰዱ በኋላ እስካሁን የገቡበት አለመታወቁን ገልጸዋል። በተመሳሳይ በደቡብ ጎንደር ጭልጋ ወረዳ የመኢአድ ሰብሳቢ የነበሩት ሻምበል ንጉሴ ደርሶ በእስር ቤት ከፍተኛ እንግልት ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የኢትዮጵያ ህዝብ ወያኔ/ኢህአዴግን አጥብቆ እንደሚጠላ የኢህአዴግ ሰነዶች አመለከቱ

የኢትዮጵያ ህዝብ ገዢዉን ፓርቲ ወያኔ/ ኢህአዴግን ከምንም ነገር በላይ እንደሚጠላ ከወያኔ ከራሱ እየሾለኩ የሚወጡ መረጃዎች ያሳያሉ። በቅርቡ በአማራ ክልል ለሚገኙ አመራሮችና አባላት የተደረገውን ስልጠና አስመልክቶ ከብአዴን ጽህፈት ቤት በቁጥር ብአዴን 145/10/ኢህ/06 ለኢህአዴግ ጽ/ቤት አዲስ አበባ በሚል የተጻፈው ደብዳቤ "አብዛኛው ህዝብ አሁንም ለመንግስት ከፍተኛ ጥላቻ" ማሳየቱን ገልጿል። የኢትዮጵያ ህዝብ ቀድሞዉንም ቢሆን አፋ በወያኔ ጠመንጃ ተለጉሞ ነዉ እንጂ ወያኔን መዉደድ ቀርቶ አንደ ወገን ያየበትም ግዜ የለም። ወያኔም ቢሆን እስካሁን በተግባር እንዳየነዉ ለኢትዮጵያ ለራሷና ለህዝቧ ምንም ደንታ የሌለዉ ባዕድ አካል መሆኑ ታይቷል።

ብአዴን አመራር እና አባላቱ ከሰላም የዘለለ የልማት ለውጥ አለመምጣቱን፣ ኢህአዴግ ቢቀጥል ባይቀጥል ግድ እንደሌላቸው፣ እንዲሁም መንግስትን በትክክለኛ ዋጋው ሳይሆን በፍርሃት እንደሚያመሰግኑ በሰነዱ ላይ ተዘርዝሮ ቀርቧል። "የኢትዮጵያ ህዝቦችና አገራዊ ህዳሴያችን" በሚለው የማጠቃለያ ግምገማ ሰልጣኞቹ " ስለአገሪቱው ታሪክ ብዙ ትምህርት መቅሰማቸውን፣ የህዳሴውን ጉዞ ለማሳካት ድርጅቱ እየከፈለ ያለውን መስዋትነት፣ የኢትዮጵያ ገናና ስልጣኔ ለምን እንደወደቀ፣ የህዳሴ ጉዞውን ሊያሳካ የሚችል መንግስት ያለ መሆኑን፣ የብዝሀነትና እኩልነት ሀገራዊ ጠቀሜታ ፣ የአማራ ገዢ መደብ ሌሎች ብሄሮችና ብሄረሰቦችን ብቻ ሳይሆን አማራውን ጭምር እንደጨቆነ" የሚያሳይ ትምህርት መውሰዳቸውን ሰነዱ ያመለክታል። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## አንድነት የአዋሳ ዉስጥ የጠራዉ የተቃዉሞ ሰልፍ በእስር ተጀምሮ በእስር ተጠናቀቀ ተሰማ

የሚሊዮኖች ድምጽ ለመሬት ባለቤትነት በሚል መሪ ቃል አንድነት ፓርቲ በአዋሳ ዉስጥ ለማካሄድ አስቦት የነበረው የተቃዉሞ ሰልፍ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የሰልፉን አስተባባሪዎችና የፓርቲውን የአመራር አባላት ብሰብስቦ በማሰሩ ሳይካሄድ መቅረቱን አዋሳ ዉስጥ የሚገኙት የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢዎች በላኩልን ዜና ገለጹ። የአንድነት ፓርቲ ሰልፉን ከማካሄዱ ከአንድ ቀን ቀደም ብሎ ባካሄደዉ የቅስቀሳ የሰልፍ ጥሪ ክፉኛ የተደናገጡት የአዋሳ ባለስልጣኖች የፖሊስ ኃይላቸዉን በመላክ በቅስቀሳ ስራ ላይ ተሰማርተዉ የነበሩትን የፓርቲዉን አባላትና ደጋፊዎች ፖሊስ አባላት 37 የሚሆኑ በቅስቀሳ ላይ የተሰማሩ አመራሮችንና ደጋፊዎችን ይዘው በተለያዩ እስር ቤቶች አስረዋቸዋል።

በማግስቱ እስረኞችን ለመጠየቅና ስንቅ ለማቀበል ከሄዱት መካከልም አንዳንዶች መታሰራቸውን በስፍራው የሚገኘው የአንድነት ፓርቲ የአዲስ አበባ ህዝብ ግንኙነት ሃላፊ አቶ ያሬድ አማረ ለኢሳት ገልጸዋል።ከአዲስ አበባ የሄዱና የአዋሳ የፓርቲው አመራሮች ፍርድ ቤት ሳይቀርቡና ክስ ሳይመሰረትባቸው በመታሰራቸው የረሀብ አድማ ያደረጉ ሲሆን፤ ዛሬ ሰኞ ፍርድ ቤት ይቀርባሉ ተብሎ እየተጠበቀ መሆኑን አቶ ያሬድ አክለው ተናግረዋል። ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የወያኔን የጥፋት ድግስ እናምክን!

ኢትዮጵያን የሚገዛው ጉጅሌ ሀገራችንን እየወሰደበት ያለው አደገኛ አቅጣጫ አሳሳቢ ከመሆን አልፎ የአደጋውን መራራ ፍሬ ማየት ከጀመርን ሰነበትን። የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ወሳኝ ከሆነው የወደፊቱ የጋራ ጥቅማቸውና ህልውናቸው በበለጠ ልዩነታቸውና ያለፈ ታሪካቸው እንደዋናው ነገር እየተቆጠረ ለሚሰበከው ስብከት የኢትዮጵያ ህዝብ አስተዋይ ባይሆን ኖሮ እስካሁን ብዙ ጥፋት በደረሰ ነበር።

ህወሃት በህዝቡ ውስጥ የኖረውን ልዩነት የጠብ፣ የግጭትና የመፈራራት መሰረት በማድረግ በሥልጣን ላይ ለመቆየት ካለው ምኞት የተነሳ በመደዴ ካድሬዎቹ አማካኝነት ለዘመናት አብሮ የኖረውን ህዝብ በማቃቃር እኩይ ተግባር ላይ ተጠምዶ ይገኛል።

ህወሃት ይህን የማጋጨት ስራ በተለይ በስልጣን የመቆየት ፍርሃት ባባነነው ቁጥር የሚጠቀምበት መሳሪያ አድርጎታል። በባህርዳር ላይ የብሄረሰቦች ኳስ ጭዋታ ውድድር ምክንያት አድርጎ፣ መደዴ ካድሬዎቹን አሰማርቶ ስታዲዮም ውስጥ ኦሮሞዎች እንዲሰደቡ ካደረገ በኋላ ነገሩን ከማረጋጋት ይልቅ በኦሮሞኛ የቴሌቪዥንና ሬድዮ፣ ኦሮሞዎች በአማራዎች ተሰደቡ ብሎ ያስነገረው ለምንድን ነው? ከዚያ በኋላ በኦሮሚያ የተለያዩ አካባቢዎች ቁጣና ጠብ ለመቀስቀስ ብሎም በዚህ ጠብ ውስጥ ገላጋይ በመምሰል የአንዱ ብሄር ጠባቂ መስሎ ለመታየት ጉዳዩን ባልተረዱ የዋሆች ውስጥ ለመግባት ይፈልጋል። በአማራ ተወላጆች አካባቢ እኛ ከሌለን ኦሮሞ ይፈጇቿኋል፤ በኦሮምያም በሶማሊያም እንዲሁ በተዘጋ በር ውስጥ በተቃራኒው ዘረኝነትንና መከፋፈልን በመስበክ ንጹሃኑ ህዝብ ከፍርሃት ተነስቶ ተገኘ ደጋፊዎቹ እንዲሆኑ በማድረግ ላይ መሆኑንም ያልገባቸው የዋሆች ይኖራሉ። ህወሃትንና ባህርዩን በቅጡ ለምናውቀው ወገኖች ግን ይህ ተንኮሉ ትልቅ ሚስጥር አይደለም።

የጉጅሌው ቡድን የራሱን ስልጣንና የዝርፊያ ኢኮኖሚ ኮርቻ ለማደላደል እስከረዳው ወይም የሚረዳው መስሎ እስከታየው ድረስ ደሃ ገበሬዎችን ማፋጀትን፣ ህዝብን እርስበርስ ማናከስን፣ የቂም መርዝ መዝራትን የሚያየው እንደ ፖለቲካ ጥበብ ነው።

ጉጅሌው ብልጠት መስሎት የጎሰኝነትንና የማንነትን ደመነፍስ የሚነካ ፕሮፖጋንዳ በህዝቡ ውስጥ በመንዛት ሊያደርስ የፈለገው ጥፋት በአብዛኛው ህዝብ ዘንድ ስላልሰራለት የራሱን ሎሌዎችና ተካፋይ መደዴ ካድሬዎችን በማሰማራት የጭካኔ ስራዎችን በማካሄድ ላይ መሆኑን በብዙ መረጃዎች አረገጋግጠናል። በአሁኑ ወቅት በየቦታው የሚካሄደውን የህዝብ ማፈናቀልና ግጭት የሚመራው ራሱ ህወሃት ያሰማራቸው ካድሬዎች እንጂ በራሱ በህዝቡ ተነሳሽነት እንዳልሆነ ሁላችንም ልናውቅ ይገባል። በዚህ ሳይጣናዊ አካሄድ ለምትደርሰው ለያንዳንዷ ጉዳት ሀላፊነት የሚወስደውም ራሱ ህወሃት መሆኑን ግንቦት 7 አጥብቆ ያምናል።

ህወሃት መቃብር አፋፍ ላይ ሆኖ የሚደግስልንን የጥፋት ድግስ ለማምከን የየብሄረሰቡ ልሂቃን ሁሉ አንድ ላይ ሆነን ህዝባችንን እንድንታደግ ግንቦት 7 ለሁሉም የነጻነት ሃይሎች ጥሪውን ያቀርባል።

ግንቦት 7 በዚህ የህወሃት የጨለማ መንገድ ላይ የሚያበራውን የብርሃን ችቦ ይበልጥ በማብራት ላይ ይገኛል። ሁላችንም በምናገኘው የብርሃን ሃይል ጨለማው ላይ እያበራን ከማሳየት አልፈን ወደ መቃብሩ ልንገፋው ይገባል።

ግንቦት 7 በኢትዮጵያ የማንነትና የብሄር ብሄረሰብ ጉዳዮች በሰለጠነ መንገድ እና በመደማመጥ ሁሉንም ተጠቃሚ በሚያደረግ መንገድ መፍታት እንደሚቻል ያምናል። ይልቁንም የወደፊቱ የህዝባችንና የሀገራችን ጥቅም ይበልጥ የሚከበረው በስብጥርነታችን ላይ በምንገነባው አንድነት መሆኑን ያምናል።

የተከበራችሁ የአገራችን ዜጎች የነጻነታችን ጊዜ ቅርብ ነው። ህወሃት መቃብር አፋፍ ላይ ሆኖ ያዘጋጀልንን የጥፋት ድግስ፣ ሀገራችን የጋራ ጠላት በመጣባት ጊዜ ሁሉ እንደምታደርገው በአንድ ላይ ታግለን የጋራ ታሪክ እንሰራ ዘንድ የዘወትር ጥሪያችን እናቀርባለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## ፋሽስቱ ወያኔ የመኢአድ አባላትን እስርና ግድያና

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

እየተፈጸመባቸው እንደሚገኙ የገለጸው መኢአድ በየክልሉና በየወረዳው በሚገኙ አባላቶቻቸውም ላይ የሚደርስባቸው ግድያ እስርና ወከባ በአስቸኳይ እንዲቆም ፓርቲው ጠይቋል። የመኢአድ የህዝብ ግንኙነት የሆኑት አቶ ተስፋሁን አለምነህ በበኩላቸው ለጋዜጣው እንደገለፁት ከአንድ ወር በፊት በአቃቂ ነዋሪና የአዲስ አበባ የመኢአድ ድርጅት ጉዳዮች ሃላፊ የነበሩት አቶ ጥጋቡ ደበላ ባልታወቀ ምክንያት ቤታቸው ውስጥ ተገድለው መገኘታቸውንና አስከሬናቸውም ከሁለት ቀን በኋላ መገኘቱን አስታውሰዋል። በደቡብ ጎንደር ይፋግ ቀበሌም የመኢአድ አባል በሆኑት አቶ ሞላ ወረታ በተባሉ ግለሰብ በጉጅሌው ወያኔ የአካባቢው ቅጥረኛ ታጣቂዎች በተፈጸመባቸው ድብደባ ግንቦት 9 2006 ኢ.ም ህይወታቸው ማለፉን አመልክተዋል። በአላማጣ ከተማም የመኢአድ አባል የሆኑት መ/ር እያሱ ሁሴን በእስር ላይ እንደሚገኙ የህዝብ ግንኙነት ሃላፊው ጨምረው ገልጸዋል።

በሌላ ዜና የሚሊዮኖች ድምጽ ለመሬት ባለቤትነት በሚል አንድነት ፓርቲ በአዋሳ ሊያካሂደው የነበረው የተቃውሞ ሰልፍ ፣ የሰልፉ አስተባባሪዎችና የፓርቲው የአመራር አባላት በመታሰራቸው ምክንያት ሳይካሄድ መቅረቱ ታውቋል። ሰልፉ ከመካሄዱ አንድ ቀን ቀደም ብሎ በፓርቲው ቅስቀሳ የተደናገጡት የጉጅሌው ወያኔ የአዋሳ ሹማምንት በፌደራል ፖሊሶች አማካኝነት 37 የሚሆኑ በቅስቀሳ ላይ የተሰማሩ የአንደነት አመራሮችንና ደጋፊዎችን ይዘው በተለያዩ እስር ቤቶች አስረዋቸዋል። አንድነት ፓርቲ በተለያዩ ክልሎች እየዞረ በርካታ ህዝብ የሚሳተፍበት የተቃውሞ ሰልፎችን እያደረገ ሲሆን በአዋሳው የተቃውሞ ሰልፍ በኦሮሞ ተወላጅ ወጣቶች ላይ የተወሰደው እርምጃ፣ የኑሮ ውድነት፣ ከማንነት ጋር በተያያዙ ችግሮችን፤ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት እና የመሳሰሉት ጉዳዮች ይነሳሉ ተብሎ ይጠበቅ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል።

አንድነት ፓርቲ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ አፈናና ፀረ-ሕዝብ አቋም በመላው ኢትዮጵያ የተዘረጋ ቢሆንም ፓርቲያችን በእንቅስቃሴዎቹ ውስጥ እንደታዘበው በደቡብ ክልል በተለየ ሁኔታ ተጠናክሮ ቀጥሏል በማለት የገለጸ ሲሆን ፓርቲያችን በተለየ ሁኔታ በደቡብ ክልል እየታየ ያለውን የአገዛዙ አፈናና ጸረ ህግ አቋም ለመገርሰስ ትግላችንን አጠናክረን እንቀጥላለን ብሏል።

## የኢትዮጵያ ህዝብ ወያኔ/ኢህአዴግን አጥብቆ እንደሚጠላ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በስልጠናው የብአዴን ታሪክ አብሮ መቅረቡንና ሰልጣኞችም የብአዴንን ታሪክ በማወቃቸው መርካታቸውን ሰነዱ አክሎ ይዘረዝራል።“ግልጽነት ያልተያዘባቸውና በተግባራዊ እንቅስቃሴ ተከታታይ ውይይትና ስራ የሚጠይቁ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?” በሚለው ንዑስ ርእስ ስር ደግሞ ”አሁንም ድረስ ብአዴንን የማይቀበሉ እና ከ97 ጋር በተያያዘ በመንግስት ላይ ተቃውሞ የሚያሰሙ ድምጾች አሉ፣ ነገር ግን የመንግስትን የሃይል እርምጃ ተከትሎ በፍራቻ እንዲኖሩ ማድረግ ተችሎአል።” ሲል አስቀምጧል።

“በውይይቱ ወቅት የታዩ የአመለካከት ችግሮች ምንድን ናቸው?” በሚለው ንዑስ ርዕስ ስር በርካታ ችግሮች ተዘርዝረው ቀርበዋል። ” በ1989 ዓም የነበረው የመሬት ክፍፍል ለቢሮክራቶች ለምን 4 ቃዳ መሬት ተሰጠ? በአማራ ክልል ብቻ የአርሶ አደር መሳሪያ ለምን ተነጠቀ? ልማቱ ወደ ትግራይ ይሄዳል፣ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት አስመራንና አሰብን መያዝ ነበረብን” የሚሉት ጥያቄዎችና አስተያየቶች በሰልጣኞች መቅረቡን ያወሳል። ሰነዱ በስልጠናው የታዩ ደካማና ጠንካራ ጎኖችንም ይዘረዝራል። ሰልጣኙ እርስ በርስ በመተጋገዝ፣ በመማማር ተሞክሮውን በማካፈልና በመተራረም የነበረው ሁኔታ በሚለው ንዑስ ርእስ ስር ደግሞ ” አሁንም ለመንግስት ህዝቡ በአብዛኛው ጥላቻ ማሳየቱ” የሚል ሰፍሮአል። የብአዴን አመራርና አባላት ”በአብዛኛው ከሰላም የዘለለ የልማት ለውጥ የለም” ብለው እንደሚያምኑ፣ “ኢህአዴግ ቢቀጥል ባይቀጥል ደንታ እንደማይሰጣቸው”፣ እንዲሁም “መንግስትን በትክክል ዋጋ ሳይሆን በፍርሃት እንደሚያመሰግኑ” በሰነዱ ማብቂያ ላይ ተገልጿል።

# እያበበ የመጣዉ ህዝባዊ ትግል

ኢትዮጵያ ህዝብ ለብዙ ዘመናት እንወድህለን በሚሉት ነገስታት ተረግጧል፤ ህብረተሰብዓዊነት አመጣንልህ ባሉት ወታደራዊ አምባገነኖችም ለ17 አመት እጅና እግሩን ታስሮ ተገዝቷል። እነዚህ ሁለት ለህዝብ ደንታ የሌላቸዉ መንግስታት ተራ በተራ በህዝብ ትግል ተንኮታኩተዉ የታሪክ ቅርጫት ዉስጥ ገብተዋል፤ ሆኖም ሁለቱንም መንግስታት በመራራ ትግል አሸንፎ የጣለዉ የኢትዮጵያ ህዝብ የትግሉን ዉጤት ማስጠበቅ ባለመቻሉ ይህ ኃያልና የረጂም ዘመን ታሪክ ባለቤት የሆነ ህዝብ ዛሬም ነፃ አወጣንህ በሚሉት ዘረኛ አምባገነኖች እየተረገጠ ነዉ። አዎ! የኢትዮጵያ ህዝብ ዛሬም እየተረገጠ ነዉ። ዛሬም አየታሰረ ነዉ። ዛሬም እየተገደለ ነዉ። ዛሬም ይህንን ሁሉ በደል የሚያደርሱበትን የአንድ ወንዝና የአንድ መንደር ምርት የሆኑ ዘረኛ አምባገነን ገዢዎችን ከጭንቅላቱ ላይ ለማዉረድ እየታገለ ነዉ። በእርግጥም የኢትዮጵያ ህዝብ ከምን ግዜም በተለየ መልኩ የወያኔን ዘረኛ አገዛዝ አምርሮ እየታገለ ነዉ፤ በተለይ በዚህ በያዝነዉ አመት ወያኔንና ሃያ ሁለት አመት ሙሉ የገነባዉን ዘረኛ ስርዐቱን ለመደምሰስና ኢትዮጵያ ዉስጥ በፍትህና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ስርዐት ለመገንባት የሚደረገዉ የሞት የሽረት ትግል ተጠናክሮ ቀጥሏል።

ወያኔ እግሩ አዲስ አበባን ከረገጠበት ግዜ ጀምሮ የጭቆና ተቋሞቹን በየቦታዉ ተክሎና ተደላድሎ ህዝብን እንዳሰኘዉ መርገጥ እስከጀመረበት ግዜ ድረስ አንዴ ሰዉ በላዉን የደርግ ስርዐት አስወገድኩላችሁ እያለ ሌላ ግዜ ደግሞ ፌዴራል ስርዐት መስርቼ ብሄር ብሄረሰቦችን ነፃ አወጣሁ እያለ ለተወሰነ ግዜም ቢሆን የኢትዮጵያን ህዝብ ቀልብ መሳብ ችሎ ነበር። ሆኖም ብዙም ሳይቆይ ያ በፌዴራሊዝም፤ በዲሞክራሲና በይስሙላ ምርጫ የተሸፈነዉ የወያኔ አስቀያሚ ገበና ይፋ እየሆነ መጥቶ ወያኔ አርግጫዉንና ግድያዉን የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ ትግሉን፤ እስሩንና ስደቱን ተያያዙት።

የወያኔን መሰሪ አላማ ገና ከጧቱ የተረዱ ኢትዮጵያዉያን ባለፉት ሃያ ሦስት አመታት ይህንን መሰሪ አገዛዝ በተደራጀ፤ ባልተደራጀ፤ በተባበረና በተበታተነ መልኩ ሲታገሉ ቆይተዋል። ሆኖም የአገራችንን የፖለቲካና የኤኮኖሚ መዋቅሮች ሙሉ ለሙሉ ከሚቆጣጠረዉ ወያኔ ጋር በቁጥር፤ በአይነትና በይዘት የሚመጥን ትግል ማካሄድ ባለመቻላቸዉና እንዲሁም ብትራቸዉን ወያኔ ላይ ብቻ ከመሰንዘር ይልቅ እርስ በርስ ስለሚላተሙበት ምንም አይነት ህዝባዊ ድጋፍ በሌለዉ ወያኔ ላይ የትግል የበላይነት ማግኘት አልቻሉም፡፡ ወያኔም እኛዉ ዉስጥ ከመካከላችን የበቀለ እሾክ በመሆኑና ደካማ ጎናችንን በሚገባ ስለሚያዉቀዉ በዚሁ ደካማ ጎናችን እየገባና እርስ በርስ እያባላን የስልጣን ዘመኑን እስከዛሬ ማራዘም ችሏል።

ወያኔ የአንድን አካባቢ ህዝብ ከሌላዉ አካባቢ ህዝብ፤ አንዱን የህብረተሰብ ክፍል ከሌላ የህብረተሰብ ክፍል ጋር በሆነዉ ባልሆነዉ ምክንያት እየፈጠረ ማጋጨቱን አሁንም አላቆመም፤ እንዲያዉም ይበልላችሁ ብሎ በስፋት እንደቀጠለበት ነዉ። ዘንድሮ ግን ህዝብ፤ የተቃዋሚ ኃይሎችና በወያኔ ተንኮል ተታልለዉ የእርስ በርስ ሽኩቻ ዉስጥ ገብተዉ የነበሩ የህዝብ ወገኖች ሁሉ የወያኔን የከፋፍለህ ግዛዉ ደባና ሴራ በሚገባ ያወቁ ይመስላል። ለምሳሌ በቅርቡ አምቦና በተለያዩ የኦሮሚያ ክልል ዩኒቨርሲቲዎች ዉስጥ ከፍተኛ ፀረ ወያኔ የተቃዉሞ ሰልፍ በተካሄደ ግዜ የወያኔ ካድሬዎች የኦሮሞ ህዝብ ቁጣና መነሳሳት አቅጣጫዉን ቀይሮ በትግል አጋሩ በአማራ ህዝብ ላይ እንዲያተኩር ለማድረግ ያልፈነቀሉት ዲንጋይ አልነበረም። ሆኖም ወያኔን ከስልጣን ለማባረርና የአገራችንን ወደፊት በህዝብ እጅ ላይ ለማስቀመጥ ቁልፉ መተባባርና አንድ ላይ መቆም መሆኑን የተረዳዉ የኦሮሞና የአማራ ህዝብ ቁጣ ይበልጥ በወያኔ ላይ ነደደ እንጂ አንደቀድሞዉ ለወያኔ የተንኮል ሴራ እጁን አልሰጠም።

ወየኔን በተለያዩ የትግል ስልቶች የሚፋለሙ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎች በፀረ ወያኔ አቋማቸዉና በአላማቸዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ሙሉ ድጋፍ ከጎናቸዉ እንዳለ እንኳን እኛ ወያኔም በሚገባ ያዉቃል። ህዝብን የመሰለ እንደ ዉኃ ማጥለቅለቅ የሚችል ኃይል ከጎናቸዉ ያሰለፉ ድርጅቶች ደግሞ ወያኔን የመሰለ ምንም ህዝባዊ መሰረት የሌለዉን ኃይል ቀርቶ ፊታቸዉ ላይ የቆመን ምንም አይነት ኃይል ከማሸነፍ የሚገታቸዉ ምንም ነገር የለም።

ሆኖም ዉኃም ቢሆን ምን ያክል ኃይለኛ መሆኑ የሚታወቀዉ ተገድቦ ወደ ተፈለገበት አቅጣጫ እንዲሄድ ሲደረግ ነዉና የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎችም ከጎናቸዉ የቆመዉን ህዝብ አስተባብረዉ አገራችንን ወደ ድል መምራት የሚችሉት መጀመሪያ እነሱ ተባብረዉ ህዝብን በአንድ አላማና በአንድ አመራር ስር ማሰለፍ ሲችሉ ብቻ ነዉ። ዛሬ በሁሉም አካባቢዎች ባይሆንም አገር ዉስጥና ካገር ዉጭ በተለያዩ አካባቢዎቾ ይቅናችሁ በሚያሰኝ መልኩ ጎልተዉ የሚታዩ ብዙ የትብብርና የትግል ቅንጅት ጅምሮች አሉ። በገበሬዉና በሰራተኛዉ፤በወጣቱና በወታደሩ በተለይ ደግሞ በተለያዩ ብሄረሰቦችና በተለያዪ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ከመለያየት ይልቅ የመቀራረብ፤ ከመወቃቀስ ይልቅ የመወያየት ከመጠላለፍ ይልቅ የመተቃቀፍ አዝማሚያዎች በብዛት እየታዩ ነዉ።

ከ1997ቱ ምርጫ በኋላ ጀምሮ እስከቅርብ ግዜ ድረስ የተቃዋሚዉን ጎራ በተለይም አገር ዉስጥና ከአገር ዉጭ የሚገኙትን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ልህቃን ለሁለት ከፍሎ ሲያጨቃጭቅ የከረመዉ ወያኔን በህዝባዊ አመጽ ወይስ በህዝባዊ እምቢተኝነት ታግለን እናዉርደዉ የሚለዉ ጥያቄ ዛሬም ድረስ አዎንታዊ እልባት ባያገኝም ዛሬ ሌላ ቢቀር እንደቀድሞዉ የተቃዋሚዉን ጎራ ለሁለት ከፍሎ የወያኔ መጠቀሚያ ማድረግ አይችልም። የኢትዮጵያ ህዝብም እኔ ያለሁት ጉድጓድ ዉስጥ ነዉና ወይ ተደጋግፋችሁ አዉጡኝ አለዚያም በቻላችሁትና በሚታያችሁ መንገድ አዉጡኝ ነዉ የሚለን እንጂ በኛ መጨቃጨቅ የሱ የጉድጓድ ዉስጥ ቆይታ ዬትየለሌ እንዲሆን አይፈልግም። ዛሬ ይህንን ተደጋግፋችሁ ነጻ አዉጡኝ የሚለዉን የኢትዮጵያ ህዝብ ጥሪ ሰምተዉ በየጫካዉና በየበረሃዉ ከወያኔ ጋር የሞት የሽረት ትግል ለማድረግ የቆረጡ ኃይሎች የሚያደርጉት መሰባሰብና በተባበር ወገንን እጅግ የሚያበረታታ ጠላትን ደግሞ ያንኑ ያክል የሚያንቀጠቅጥ መልካም ጅምር ነዉ።

ከተለያዩ የአገራችን ኣካባቢዎችና ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ተዉጣጥተዉ ወያኔን በሚገባዉ ብቸኛ ቋንቋ ለማነጋገር ቆርጠዉ የተነሱት የኢትዮጵያ ልጆች ወያኔን አንከባልለዉ የሚጥሉት ባነገቡት ጠመንጃ ብቻ ሳይሆን በህብረታቸዉና በአላማ ጽናታቸዉ እንደሆነ በሚገባ ያዉቃሉ። ለዚህም ነዉ ዛሬ እነዚህ ጀግኖች ባሉበት ጫካና በረሃ ሁሉ የሚሰማዉ መዝሙር . . . . ላንቺ ነዉ ኢትዮጵያ . . . ላንቺ ነዉ... ላንቺ ነዉ ኢትዮጵያ ላንቺ ነዉ... ላንቺ ነዉ ኢትዮጵያ ደሜን የማፈሰዉ የሆነዉ።

ዛሬ አገራችን ኢትዮጵያን ከዘረኞችና እነሱ ከገነቡት ዘረኛ ስርዐት ለማላቀቅ ዉስብስብነት ገብቷቸዉ ይህንን ዉስብስብ ትግል ከመታገል ዉጭ ሌላ ምንም አማራጭ እንደሌለ ተረድተዉ የትግል ህብረትና አንድነት የጀመሩ ብዙ ወገኖች አሉ። ይህ የሚያበረታታና ተስፋዉ የለመለመ ጅምር የሁላችንም ድጋፍና ተሳትፎ የሚያስፈልገዉና አለንልህ ሊባል የሚገባዉ አገራዊ ጅምር ነዉ። በዚህ ጅምር ዉስጥ ትንቅንቅ አለ፤ በዚህ ጅምር ዉስጥ መስዋዕትነት አለ፤ በዚህ ጅምር ዉስጥ ድል አለ። በህዝባዊ እምቢተኝነቱ ጎራ ከቅርብ ግዜ ወዲህ በብዙ የኢትዮጵያ ከተማዎች ዉስጥ ህዝቡ የወያኔን ግልምጫ፤ እስርና ድብደባና ግድያ ከምንም ባለመቁጠር በየአደባባዩ ወያኔን ፊት ለፊት መጋፈት ጀምሯል። ወያኔን በብዕራቸዉ የሚታገሉ ወጣቶችም ከዘላለም ባርነት የአንድ ቀን ነጻነት ይሻለናል ብለዉ በሰላ ብዕራቸዉ ህዝብን እንዳስተማሩ ቃሊቲ ወርደዋል። በህዝባዊ አመጹ ጎራ ደግሞ የአባቶቹን ታሪክ ለመድገም ቆርጦ የተነሳዉ የኢትዮጵያ ወጣት አዲሱን የኢትዮጵያ የፍትህ፤ የነጻነትና የእኩልነት ታሪክ በደሙ ለመጻፍ የከተማ ኑሮ በቃኝ ብሎ የጫካና የበረሃ ኑሮዉን ተያይዞታል።

ዛሬ ይህንን እንዳባቶቹ ዱር ቤቴ ብሎና ጠመንጃቸዉን አንግቦ ከወያኔ ጋር ትንቅንቅ የጀመረዉን ህዝባዊ አርበኛ የብሄረሰብ ስብጥር የተመከለተ ማንም ሰዉ የአገራችን ኢትዮጵያ ዳግማይ ትንሳኤ ደጃፍ ላይ መሆኑን በሙሉ አፉ ደፍሮ መናገር ይችላል። ወያኔ በነጋ በጠባ ከሚያስረዉና የወደፊቱን ካጨለመበት ወጣት ጀምሮ ገዳማቸዉን ካፈረሰባቸዉ መነኮሳትና ቤ/ክርስቲያናቸዉን አስካረከሰባቸዉ ካህናት ድረስ የትግሉ ጎራ ሁሉንም አይነት ኢትዮጵያዉያን በብዛት አካትቶ ይዟል።

ወያኔ ስልጣን እንደያዘ በሚቆይባት በእያንዳንዷ ቀን ተጨማሪ ወጣቶች እንደሚታሰሩ፤ተጨማሪ ሰላማዊ ሰልፈኞች እንደሚገደሉ፤ተጨማሪ ጋዜጠኞች ሽብርተኞች ተብለዉ እንደሚታሰሩ፤ ተጨማሪ ምሁራን አገራቸዉን ለቅቀዉ እንደሚሰደዱና የአገራችን የኢትዮጵያም አንድነት የበለጠ እየላላ እንደሚሄድ ሁላችንም በሚገባ እናዉቃለን። በሌላ አነጋገር ወያኔ ስልጣን እንደያዘ የመቆየት አንድ ተጨማሪ ቀን በሰጠነዉ ቁጥር የኛም ሆነ የአገራችን ህልዉና በቀላሉ የማናበጀዉ እጥፍ ድርብ ችግር ዉስጥ ይወድቃል። ይህ እናት አገራችን ኢትዮጵያ ላይ የተደቀነዉ ችግርና መከራ ገና ከጧቱ የታያቸዉ ኢትዮጵያዉያን ባለፉት ሃያ አመታት የየራሳቸዉን እርምጃ ሲወስዱ ቆይተዋል። በዚህ ሂደት ዉስጥ አንዳንዶች ዉድ ህይወታቸዉን ገብረዋል፤ ሌሎች ደግሞ ታስረዋል፤ ተደብድበዋል፤ አገር ለቅዉ ተሰድደዋል። እዚህ ላይ አንድ ሁላችንም በትክክል ልንገነዘበዉ የሚገባን ሀቅ አለ፤ እሱም የኢትዮጵያ ችግር የአንድና የሁለት ሰዉ ችግር አይደለም፤ በአንድና በሁለት ሰዎች የሚፈታ ችግርም አይደለም። ኢትዮጵያ የሁላችንም አገር ናት፤ ችግሩም የሁላችንም ነዉ፤ ወያኔን በቆራጥነት ታግለን አገራችንን ከመበታተን ህዝባችንን ደግሞ ከዘረኝነትና ከድህነት ማላቀቅ ያለብንም እኛዉ ነን። ወያኔ ስለጠላነዉ፤ ስለሰደብነዉ ወይም ስለጮህንበት ብቻ በህዝብና በአገር ላይ በደል መፈጸሙን አያቆምም፡፡ እነዚህ በደሎችና ችግሮች የሚቆሙትና የኢትዮጲያ ህዝብ የሰላም አየር መተንፈስ የሚችለዉ ወያኔ ከስልጣን ሲወገድና በምትኩ ኢትዮጵያዉያንን በእኩልነት የሚያስተናግድ መንግስት በኢትዮጵያዉያን ተመርጦ ስልጣን ሲይዝ ብቻ ነዉ።

( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የደገሃቡር የጸጥታ አዛዥ ተገደሉ

ኦብነግ በሚል ምህጻረ ቃል የሚጠራዉና ለኦጋዴን ህዝብ መብትና ነጻነት መከበር የሚታገለዉ ታጣቂ ኃይል ባለፈዉ ሳምንት በደጋሃቡር ላይ ድንገት አሸምቆ በወሰደዉ የማጥቃት እርምጃ የወያኔን የጸጥታ ኃይሎችና የክልሉን የጸጥታ ጉዳዮች ሃላፊ መግደሉን አሳወቀ። የኦጋዴን ክልል የጸጥታ ጉዳዮች ሃላፊ የሆኑት አቶ አሻር በታጣቂዎቹ በተተኮሰባቸዉ ጥይት ቆስለው ወደ ደጋሃቡር ሆስፒታል ከተወሰዱ በኋላ በበነጋታዉ ጠዋት ማረፋቸውን የደረሰን ዜና አመልክቷል። ከእሳቸዉ በተጨማሪ የአካባቢው የልዩ ሚሊሺያ አዛዥ የሆኑት ሙሃመድ ዳይክ ከፉኛ ቆስለው አሁንም በሆስፒታሉ በመታከም ላይ ሲሆኑ፣ አማጽያኑ ጥቃቱን ፈጽመው ከአካባቢው መሸሻቸው ታውቋል።

ኢህአዴግ በክልሉ እየተባባሰ የመጣው የጸጥታ ሁኔታ ስጋት ላይ መጣሉን ተከትሎ ከኦብነግ ጋር ሊያደርገው ያሰበው ድርድር ሁለት የኦብነግ አመራሮች ናይሮቢ ኬንያ ላይ ተይዘው ከተወሰዱ በሁዋላ ተደናቅፏል። መሪዎቹ እጃቸውን በፈቃዳቸው እንደሰጡ መንግስት ቢገልጽም፣ እስካሁን ድረስ የታፈኑት መሪዎች ቀርበው እጃቸውን በፈቃዳቸው መስጠታቸውንና አለመስጠታቸውን አልተናገሩም።

በአካባቢው እየታየ ያለው ሁኔታ ያሰጋው መንግስት የክልሉን ፕሬዚዳንት ለመተካት ውስጥ ውስጡን እንቅስቃሴ ቢጀምርም፣ በአካባቢው የተሰማራው የመከላከያ ሰራዊት አዛዦች የፕሬዚዳንቱን መተካት በመቃወማቸው በመንግስት ሹሞችና በመከላከያ አዛዦች መካከል ልዩነት ተፈጥሯል። በመንግስት በኩል ያለው አቋም ፕሬዚዳንቱ አቶ አብዲ ሞሃመድ ኡመር በሚከተሉት ፖሊሲ የክልሉ ህዝብ ይበልጥ እየተከፋ ተቃዋሚዎች ደጋፊ እየሆነ ነው የሚል ሲሆን፣ በመከላከያ አዛዦች በኩል ያለው አቋም ደግሞ አቶ አብዲ ለክልሉ ጸጥታ እና መረጋጋት እጅግ አስፈላጊ ናቸው የሚል ነው። ታዛቢዎች እንደሚሉት በክልሉ ውስጥ ከፍተኛ ኢንቨስተር በመሆን እየሰሩ ያሉት የሌ/ጄኔራል ዮሃንስ ገ/መስቀል የፍቅር ጓደኛ አቶ አብዲን በስልጣን ላይ መቆየት በእጅጉ ይደግፋሉ። ከመከላከያ ባለስልጣናት ጋር የተፈጠረው ከፍተኛ የሙስና ግንኙነት አቶ አብዲ የአካባቢውን የመከላከያ አዘዦች ድጋፍ አስገኝቶላቸዋል።

ሰሞኑን አቶ አብዲ 1500 በክልሉ የሚገኙ የአገር ሽማግሌዎችን ሰብስበው የማእከላዊ መንግስት ባለስልጣናት በተለይም የደህንነት ሃላፊው አቶ ጌታቸው አሰፋ ሊያስገድላቸው እንደሚፈልግ በግልጽ ሲናገሩ ተሰምቷል።አብዛኛውን አገር ሽማግሌዎች ባስደነገጠ መልኩ፣ መንግስት እኛን ሳይሆን መሬታችንን ነው የሚፈልገው ያሉት አቶ አብዲ፣ የክልሉ ሽማግሌዎች የመንግስትን የደህንነት ሃይሎች እንዳይፈሩ መክረዋል። የደህንነት ሃይሎች ከክልላችን ተጠራርገው ወጥተዋል በማለት የተናገሩት ሹሙ፣ የደህንነት ሹሙም በሙስና የተዘፈቁ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ጅጅጋ የሚገኘው የነርሲንግ ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት ተዘግቶ ተሰብሳቢዎች ለ10 ቀናት ያክል እንዲያርፉበት የተደረገ ሲሆን፣ አቶ አብዲ አገር ሽማግሌዎች ከእርሳቸው ጎን እንዲቆሙ ከመማጸን ጀምሮ ፣ ክልሉን ሊቆጣጠሩ የሚፈልጉ ሃይሎች ካሉ አንቀጽ 39ን ተግባራዊ እስከማድረግ እንደሚደርሱ ሲዝቱ መሰማቱን ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉት የኢሳት ምንጮች ገልጸዋል።

## የሶማሌ ክልል ፕሬዚዳንት የመንግስት ደህንነቶች ሊገድሉኝ ነዉ በሚል ፍራቻ ጠባቂዎቻቸውን ቀየሩ

የወያኔ ተለጣፊ ሆኖ የሶማሌን ክልል በፕሬሲዳንትነት የሚመራዉ አብዲ ሞሃመድ ኡመር የፌደራሉ መንግስት የደህንነት ሰዎች ሊገድሉኝ ይፈልጋሉ በማለት ከዚህ ቀደም ሲጠብቁት የነበሩ ጠባቂዎቹን በመቀየር አካባቢው በታማኞቻቸው በአይነ ቁራኛ እንዲጠበቅ እያደረጉ ነው። በዚህ የተነሳ ካለፉት ሳምንታት ጀምሮ ወደ የፕሬዚዳንቱ ቢሮ ወደሚገኝበት አካባቢ የሚዘዋወሩ ሰዎች ልዩ ፍተሻ እየተደረገባቸው ነው።አቶ አብዲ ባለፈው ሳምንት ከ9 ዞኖችና ከ68 ወረዳዎች የተውጣጡ 1 ሺ 500 የሚሆኑ ከመላው ኦጋዴን የተውጣጡ የአገር ሽማግሌዎችን ሰብስበው ማእከላዊውን አስተዳደር የሚተቹ ንግግሮችን ተናግረዋል።

የደህንነት ሃላፊው ጌታቸው አሰፋ በሙስና የተበለሻ "ሌባ ነው" ሲሉ የፈረጁት አቶ አብዲ፣ ለፓስፖርት ማውጫ በሚል ከኦጋዴን ተወላጆች ገንዘብ እንደሚቀበሉ ለተሰብሳቢው ተናግረዋል። "አትፍሩ የኢህአዴግ የደህንነት ሃይል በሙሉ ከክልላችን ተጠራርጎና ተሰባብሮ እንዲወጣ አድርጌዋለሁ፣ በክልሉ ያለሁት እኔ ነኝ" በማለት የተናገሩት አቶ አብዲ፣ ማንኛውም የአገር ሽማግሌ የኢህአዴግን የደህንነት ሃይሎች እንዳይተባበር ጥሪ አቅርበዋል።

"ኢትዮጵያውያን አይወዱንም፣ መሬታችን እንጅ እኛን አይፈልጉንም፣ እንደሁለተኛ ዜጋም ያዩናል" ያሉት አቶ አብዲ፣ ህገመንግስቱ በከፍተኛ ፍርሃት ውስጥ የሚገኙት ፕሬዚዳንቱ፣ የእጅ ስልካቸውን ከመቀየር ጀምሮ በግቢያቸው ውስጥ የሚካሄዱ ማንኛውንም አይነት እንቅስቃሴ ክትትል እንዲደረግበት ትእዛዝ ሰጥተዋል። ለመንግስት ደህንነቶች ይሰራሉ ብለው የጠረጠሩዋቸውን ሰዎች ቢሮ ማዘጋታቸውም ታውቋል።በጅጅጋ አንዳንድ አካባቢዎች በተለይ እርሳቸው ጫት በሚቅሙበት ቀበሌ 6 አካባቢ ከ11 ሰአት በሁዋላ የህዝቡ እንቅስቃሴ እንዲገታ የተደረገ ሲሆን፣ ወደ ከተማዋ የሚደረጉ ፍተሻዎችም ተጠናክረዋል።

በአቶ አብዲ እና በኢህአዴግ መካከል በተለይም በደህንነት ሹሙ ጌታቸው አሰፋ መካከል ልዩነት ተነስቶ እንደነበር ኢሳት መዘገቡ ይታወሳል። በቅርቡ አልሸባብ በክልሉ በመንግስት ታጣቂዎች ላይ የፈጸመው ጥቃት በህወሃት ባለስልጣናትና በአቶ አብዲ መካከል ያለውን ልዩነት ሳያሰፋው እንዳልቀረ ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉ ወገኖች ገልጸዋል። አቶ አብዲ በከፍተኛ ስጋት ውስጥ እንዲወድቁ ያደረጋቸውም የልዩነቱ መስፋት ሳይሆን አይቀርም።

በሌላ ዜና ደግሞ አቶ አብዲ የኦጋዴን ነጻ አውጭ ድርጅት ተዳክሟል በማለት በተናገሩ ማግስት፣ ከደገሃቡር 1 ኪሜ ርቀት ላይ ኦብነግ በወሰደው ጥቃት 7 ሰዎች ተገድለው 9 ቆስለዋል።ከፉኛ ከቆሰሉት መካከል የደገሃቡር የጸጥታ ሃላፊ አቶ አሻርና የአካባቢው የልዩ ሚሊሺአ አዛዥ ሙሀመድ ዳይክ ይገኙበታል። ሁለቱም ሰዎች ሲታከሙበት ከነበረው ደገሃቡር ሆስፒታል ወደ ካራማራ ሆስፒታል እንዲወሰዱ ተደርጓል።

## የተለያዩ አለማቀፍ ተቋማት ኢትዮጵያ ውስጥ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ወይም ከጣራ ላይ ታስሮ እንደሚደበደቡ፣ እንቅልፍ እንዳያገኙ እንደሚደረግ፣ ለብቻቸው እንዲታሰሩ፣ በኤሌክትሪክ እንዲጠበሱ፣ ውሀ ውስጥ እንዲዘፈቁ፣ በብልታቸው ላይ ከባድ እቃ እንደሚንጠለጠልባቸው፣ ተገደው የራሳቸው ያልሆነውን ቃል የራሳቸው እንደሆነ አድርገው እንዲፈርሙ እንዲሁም አንዱ እስረኛ ሌላውን እንዲደበድብ ይደረጋል በማለት የአገዛዙን ጭካኔና አምባገነንነት ለአለም ህዝብ እያጋለጡ እንደሚገኙ ታውቋል።

የጉጅሌው ወያኔ ቅጥረኛ የጸጥታ ሀይሎች በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ሰዎችን ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ እንደሚገድሉ፣ በአፋር፣ በአማራ፣ በጋምቤላ፣ በሶማሊ እና በሌሎችም ክልሎች የተፈጸሙ ግድያዎችን በዋቢነት በማንሳት አመልክተዋል። ተቋማቱ በስተመጨረሻም የአለማቀፍ መንግስታት በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ለጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ እያደረጉ የሚገኙትን ማንኛውንም አይነት ድጋፍ እንዲያጤኑ አበክረው ማሳሰባቸውን ዘጋቢያችን ያደረሰን መረጃ ያመለክታል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጀል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## አንድነት የአዋሳ ዉስጥ የጠራዉ የተቃዉሞ ሰልፍ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

መድረክ በአዋሳ በከፍተኛ ወከባ ውስጥ ሆኖ የተቃውሞ ሰልፍ ማድረጉ ይታወቃል። አንድነት ፓርቲ በተለያዩ ክልሎች እየዞረ በርካታ ህዝብ የሚሳተፍበት ሰላማዊ ሰልፎችን እያደረገ ነው። በአዋሳው ሰላማዊ ሰልፍ በኦሮሞ ወጣቶች ላይ የተወሰደው እርምጃ፣ የኑሮ ውድነት፣ ከማንነት ጋር በተያያዙ የሚታዩት የሰብአዊ መብቶች ጥሰት እና የመሳሰሉት ጉዳዮች ይነሳሉ ተብሎ ይጠበቅ ነበር።አንድነት በአዋሳ ለሚያካሂደው የተቃውሞ ሰልፍ ለክልሉ መንግስት የእውቅና ደብዳቤ ያስገባው ከአንድ ወር በፊት ነበር። የከተማው ምክር ቤት እስካለፈው አርብ ድረስ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ለመስጠት እየተነጋገርነበት ነው በማለት ሲያጓትተው ቆይቷል።

አንድነት ፓርቲ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ “በተለየ ሁኔታ በደቡብ ክልል እየታየ ያለው መንግስታዊ አፈናና ጸረ ህግ አቋም እንዲገታ ትግላችንን አጠናክረን እንቀጥላለን” ብሎአል።“የስርዓቱ መንግስታዊ አፈናና ፀረ-ሕዝብ አቋም በመላ ኢትዮጵያ የተዘረጋ ቢሆንም ፓርቲያችን በእንቅስቃሴዎቹ ውስጥ እንደታዘበው በደቡብ ክልል በተለየ ሁኔታ ተጠናክሮ ቀጥሏል” ያለው አንድነት፣ “በክልሉ የሚገኙ የተለያዩ ሹማምንቶች ባደረባቸው የገዥነት መንፈስ ሰላማዊ እንቅስቃሴዎችን በማፈንና ብሎም ያለምንም ማስረጃና ምክንያት ሰላማዊ ታጋዮችን ወደ እስር ቤት በመከተት ተግባራዊ እያደረጉት ” ነው ብሎአል። በወላይታ ዞን ሶዶ ከተማ የፓርቲው ከፍተኛ አመራሮች ወደእስር ቤት መወሰዳቸውን፣ ቁጫ ላይ ተጠርቶ የነበረው ሰላማዊ ሰልፍም እንዲሁ በጉልበት፣ በእስርና አፈና እንዳይካሄድ መደረጉን የገለጸው አንድነት፤ የክልሉ ዋና ከተማ በሆነችው አዋሳ የተጠራው ሰልፍ በህገወጥ እስር መጠናቀቁን ገልጿል። “በክልሉ ለመዝጋት እየተሞከረ ያለውን የህዝብ ጥያቄ ከህዝብ ጋር በመሆን መፍትሔ እንዲያገኝ እናደርጋለን” የሚለው አንድነት ጉዳዩን ወደ ህግ እንደሚወስደውም ገልጿል።ያለምንም ወንጀል የታሰሩ አባሎቻችንና አመራሮቹ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳ እንዲፈቱ የጠየቀው ፓርቲው፣ በደቡብ ክልል እየታየ ያለውን መንግስታዊ አፈናና ፀረ-ሕዝብ አቋም እንደሚታገለው አስታውቋል። ዘግይቶ በደረሰን ዜና ደግሞ በቅስቀሳ ላይ የነበሩት አመራሮች የዋስትና መብታቸውን ተከልክለው ወደ እስር ቤት እንዲመለሱ ተደርጓል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ አዋሳ ዉስጥ የታሰሩ የአንድነት ፓርቲ አመራር አባላት የይስሙላዉ ፍርድ ቤት መቅረባቸዉ ተሰማ።ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የራሱ ህገ መንግስት የሚፈቅደዉን ሰላማዊ ሰልፍ አድርጋችኋል ወይም ያለፍቃድ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ህገወጥ ቅስቀሳ አድርጋችሁዋላ በሚል በግፍ ሰብስቦ ያሰራቸዉን የአንድነት ፓርቲ አመራር አባላት ባሳለፍነዉ ሳምንት ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ማድረጉንና እያንዳንዱ ታሳሪም የ5 ሺ ብር ዋስትና እንዲያስይዝ ከተደረገ በኋላ መፈታቱን ዘጋቢዎቻችን ከአዋሳ በላኩልን ዜና ገለጹ። የቀጠሮ ጊዜያቸው የፊታችን አርብ ቢሆንም፣ እስረኞቹ ያለቀጠሮ እንዲቀርቡ ተደርጎ ያዋስትና መብት ተፈቅዶላቸዋል። ባለፈው ሰኞ ችሎቱ የእስረኞችን የዋስትና መብት ከልክሎ ነበር። የአንድነት ፓርቲ አመራሮች ባለፈው እሁድ በአዋሳ የተቃውሞ ሰልፍ ለማድረግ ሲንቀሳቀሱ በመታሰራቸው ሰልፉ ሳይካሄድ መቅረቱን መዘገባችን ይታወሳል። ዋስትና የተጠየቁት አመራሮች የዋስትና ገንዘብ ለማስያዝ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ጉዳዩን የሚከታተሉ ወገኖች ለኢሳት ገልጸዋል።ፓርቲው በደቡብ ክልል የሚታየውን አፈና የሚያወግዝ ጠንካራ መግለጫ አውጥቷል።

## እያበበ የመጣዉ ህዝባዊ ትግል

. . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

የኢትዮጵያ ህዝብ ለሰብዓዊ መብቱ፤ ለነጻነቱና ለእናት አገሩ አንድነት መከበር ትናንት ካደረገዉ ትግል የዛሬዉ እጅጉን የሚያበረታታ ቢሆንም አሁንም ይህንን ህዝባዊ አደራ ከተሸከሙ ኃይሎች የሚጠበቅ ብዙ ስራ አለ። ከላይ ከፍ ሲል ደጋግመን እንደጠቀስነዉ ከወያኔ ጋር በሚደረገዉ የትግል ሂደት ዉስጥ የህዝብ ኃይሎች የሚመኩበት ትልቁ ኃይል ህብረታቸዉና ከጎናቸዉ የተሰለፈዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ነዉ። የተቃዋሚ ኃይሎች አለመተባበርና አለመግባባት ከጎናቸዉ በተሰለፈዉ ህዝብ ዉስጥም አለመግባባትና አለመተባበር ይፈጥራል። ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ እየተቃወምነዉና እየታገልነዉ ዛሬ ድረስ የደረሰዉ እኛ ዉስጥ የነገሰዉ አለመተባበርና አለመግባባት እየረዳዉ ነዉ። ስለዚህ ዛሬ ወያኔን ለማስወገድ ብቻ ሳይሆን ወያኔ ከተወገደ በኋላም የሚገጥሙንን ዲሞክራሲያዊ ተቋማትን የመገንባትና ህዝባዊ ስርዐትን የመፍጠር አደራ ጭምር ለመወጣት በህብረትና በአንድነት መቆም አለብን። አንድነታችንና ህብረታችን አንድ ስራ ሰርቶ ወያም አንድ ነጣላ አላማ ከግብ አድርሶ የሚቆም ሳይሆን የእኛን ሀላፊነት ተወጥተን ለልጅ ልጆቻችን የምናስተላልፈዉ ብሄራዊ ቅርስ መሆን አለበት።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!**

## እያበበ የመጣዉ ህዝባዊ ትግል